Haile Selassie I - Harar Military Academy North America

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሰሜን አሜሪካ

# ነሐሴ 9 ቀን 2026 ዓ.ም መደበኛ ስብሰባ

# ቃለ-ጉባኤ

(Minutes and Highlights of August 09, 2026  HMAHAA Bimonthly Meeting)

የቀዳማዊ ሐይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚያካሄደውን መደበኛ ስብሰባ ነሐሴ 9 ቀን 2026 በተለመደው የስብሰባ ቦታ አካሂዷል።

የሰብሰባ ቀን፦ ኦገስት 9 ቀን 2026 ዓ.ም

የስብሰባው ሰዓት፦

**ከ1፡00-2፡00** ፒ. ኤም የአባላት መሰባሰቢያ ሰዓት

**ከ2፡00-3፡00** ፒ.ኤም ምሳና የግል ጨዋታ ጊዜ

**ከ3፡00-5፡00** ሰዓት የአጀንዳ ውይይት ጊዜ

የሰብሰባ አድራሻ፦

***6601 Little River Tnpk # 200***

***Alexandria. VA 22313***

ስብሰባ አዘጋጆች፦

የእለቱን ስብሰባ ቦታና መስተንግዶ ያዘጋጁት ሻምበል በዙ ወልደሚካኤል (7ኛ ኮርስ) እና ባለቤታቸው ዶ/ር ሙሉእመቤት ከተተ ናቸው።





በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላት ብዛት፦

በስብሰባው ላይ 37 አባላት፤ 38 የቤተሰብ አባላትና እንግዶች በድምሩ 75 አባላት ተገኝተዋል። በተሳታፊዎች ብዛት እስከ ዛሬ ከተደረጉት ስብሰባዎች ሁሉ ከፍተኛ ሰው የተገኙበት ስብሰባ ነበር።

ከምሳ በፊት የነበረ ፕሮግራም

ምሳ ከመጀመሩ በፊት "እንኩዋን ደህና መጣችሁ" ሰላምታ ከቀረበ በኋላ የአዲስ እንግዶች ትውውቅ ተደርጓል። በእለቱ ብዙ እንግዶች የተገኙ ሲሆን ሁሉንም በስም መዘርዘር ባይቻልም ከሻምበል በዙና ዶ/ር ሙሉእመበት ቤተሰብና እንግዶች ሌላ የሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ ልጆችና ቤተሰቦች ተገኝተው ነበር። የማህበራችን አባል ዶ/ር መሐመድ ኑር (3ኛ ኮርስ) ለሁለተኛ ጊዜ በማህበራችን ስብሰባ ላይ ተገኝተው ራሳቸውን እንደገና አስተዋውቀዋል። የማህበሩ አባላትም እንኳን ደህና መጡ በማለት መልካም ምኞታቸውን በጭብጨባ ገልጸዋል። ከእንግዶች ትውውቅ በኋላ የማህበራችን ሊ/መንበር ኮሎኔል ጋተው ተፈሪ ለእለቱ መስተንግዶ አዘጋጆች ምስጋና ካቀረቡ በኋላ አባላት ምሳ ተጋብዘዋል።

የአጀንዳ ውይይትና ውሳኔ

ከ**3፡00-5፡00** ፒ.ኤም በነበረው ሰዓት ሁለት የተለያዩ ዝግጅቶች ተከናውነዋል።

ሀ. በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ የአጀንዳ ውይይት ጊዜ ነበር።

ለ. በሁለተኛው ፕሮግራም "ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ አሉምናይ ማህበር በሰሜን አሜሪካ" የተመሰረተበት *25ኛ ዓመት* መታሰቢያ ቀን በልዩ ሁኔታ ታስቦ ውሏል።

ሀ**.** የአጀንዳ ውይይትና የተላለፈው ውሳኔ

ለውይይት የቀረቡት የመወያያ ርእሶች የሚከተሉት ነበሩ፦

1. የአካዳሚ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ ዝግጅት ኮሚቴ ስራ ሪፖርት መስማት፤
2. የአካድሚ ምሩቃንን ስም በየኮርሱ በነሐስ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ለማስቀመጥ የተጠየቀ ገንዘብ እርዳታን የተመለከተ ውይይት፤
3. የማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስራ ዘመን በሴፕቴምበር 2026 ዓ.ም ስለሚጠናቀቅ አዲስ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለመምረጥ አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ እንዲካሄድ የቀረበ አጀንዳ፤
4. የሻለቃ/ዶ/ር ዮሐንስ አባተን (2ኛ ኮርስ አባል) ምስክርነት መስማት ናቸው።

1. አጀንዳ አንድን አስመልክቶ የቀረበው ሃሳብ የአካዳሚ ታሪክ 2ኛ እትም መጽሐፍ ለማሳተም በተወሰነው ውሳኔ መሰረት አዲስ አበባ ከተቋቋመው መጽሐፍ ዝግጅት ኮሚቴ ጋር የአካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ ማህበርን ወክሎ የሚሰራ ሶስት አባላት ያሉበት ኮሚቴ ማርች *29* ቀን *2026* በተከሄደው መደበኛ ስብሰባ መምረጣቸው ይታወሳል። ኮሚቴው የተሰጠውን ስራ አጠናቅቆ ሰኔ 30 ቀን 2026 ዓ.ም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲያቀርብና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ተቀብሎ ከገመገመ በኋላ ነሐሴ 30 ቀን 2026 ዓ.ም ለአዲስ አበባው ኢዲቶሪያል ቦርድ ለማቅረብ እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆንም ኮሚቴው በሰኔ ወር ሪፖርቱን ማቅረብ አልቻለም ነበር። ሪፖርቱን ለአዲስ አበባው ዋና ኮሚቴ ለመላክ የቀረው ከአንድ ወር

ያነሰ ጊዜ ብቻ ስለሆነ የደረሰበትን ደረጃ ኦገስት 9 ቀን 2026 ዓ.ም በሚካሄደው ስብሰባ ሪፖርቱን ለጉባኤው እንዲያቀርብ አጀንዳ ተይዞ ነበር። ነገር ግን ተመራጭ ኮሚቴው አሁንም በቂ ባልሆነ ምክንያት ሪፖርቱን በእለቱ ማቅረብ አልቻለም። መጽሐፉ የሁሉንም አካዳሚ ምሩቃን ታሪክ ማካተት የሚገባው በመሆኑ የሰሜን አሜሪካ ማህበር አባላትን አለማካተት ታሪኩን ያልተሟላ ስለሚያደርግ የተሰጠውን የስራ ሃላፊነት መወጣት ግድ ይሆናል። ስለዚህም የተሰጠውን የስራ ድርሻ ሰርቶ ለመላክ የቀረው በጣም አጭር ጊዜ ስለሆነ ምን መደረግ አለበት? የሚለው ሃሳብ ለጉባኤው ቀርቦ አባላት በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ኮሚቴ መምረጥ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሰርቶ እንዲልክ ጉባኤው በአንድ ድምጽ ውሳኔ አስተላልፏል። ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ውሳኔውን ተቀብሎ እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረው ወዲያው ነበር።

2. የእርዳታ ገንዘብ ጥያቄን በተመለከተ ለዚህ ጉዳይ የተመደበ ባጀት ባለመኖሩ ከማህበሩ ባንክ ሂሳብ ወጪ አድርጎ መስጠት ስለማይቻል አባላት የቻሉትን ያህል በግል እንዲያዋጡ በቀረበው ሃሳብ መሰረት አባላት በፈቃደኝነት መዋጮ አድርገዋል። በእለቱ አባላት ባሳዩት ከፍተኛ ተሳትፎና ሙሉ ፈቃደኝነት አንድ ሺህ ሁለት ዶላር ($1200) መሰብሰብ ተችሏል። አባላት ስላደረጉት ከፍተኛ ትብብር ኮሚቴው ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል። ገንዘቡ ከተሰበሰበ በኋላ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አዲስ አበባ ከሚገኘው የአካዳሚ ምሩቃን ማህበር ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ መጠን ከአጣራ በኋላ አምስት መቶ ዶላር ($ 500.00) እንዲላክ አድርጓል።

3. አዲስ ተሻሽሎ የወጣው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ብቻ መሆኑን ይደነግጋል። ስለዚህም በስራ ላይ ያለው ስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ የአገልግሎት ዘመኑ የሚጠናቀቀው በድሴምበር *2026* ዓ.ም ስለሆነ አዲስ ምርጫ የሚያካሂድ አስመራጭ ኮሚቴ እንዲመረጥ አጀንዳ ቀርቦ ነበር። በአጀንዳው ላይ አባላት ከተወያዩ በኋላ አዲስ ምርጫ ለማከሄድ የቀረው ጊዜ አጭር ስለሆነ በስራ ላይ ያለው ኮሚቴ ተጨማሪ ሁለት ዓመት እንዲሰራ ከቤቱ

አስተያየት ቀርቦ አባላት በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኋላ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሁለት ዓመት በድጋሚ እንዲያገለግል ሃሳብ ቀርቦ የኮሚቴው ስራ ዘመን በሁለት ዓመት እንዲራዘም ጉባኤው በአንድ ድምጽ ወስኗል።




ሊ/መንበርና ጸሐፊ በውይይት ላይ

4. የሻለቃ/ዶ/ር ዮሐንስ አባተ የሕይወት ምስክርነት

አጀንዳ ውይይቱን ቀጥሎ የነበረው ፕሮግራም የሻለቃ/ዶ/ር ዮሐንስ አባተን ምስክርነት መስማት ነበር። ዶ/ር ዮሐንስ ስለ ጦር አካዳሚው ያላቸውን ተሞክሮና ትውስታ ለማህበሩ አባላት እንዲያካፍሉ በተጠየቁት መሰረት ትውስታቸውንና ልምዳቸውን ለስብሰባው ተሳታፊዎች አካፍለዋል። ዶ/ር/ሻለቃ ዮሐንስ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ 2ኛ ኮርስ ምሩቅ ሲሆኑ ከአካዳሚ የተመረቁት እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በ1961 ዓ.ም ነበር። ዶክተር ዮሐንስ በአካዳሚ ውስጥ የሶስት አመት ስለጠናቸውን ጨርሰው ከተመረቁ በኋላ የተመደቡት በ3ኛ ክፍለ ጦር ተዋጊ መሐንዲስ ክፍል ነበር። እርሳቸው ክፍሉ ውስጥ ሲመደቡ በአቋም ደረጃ የተቋቋመ ከመሆኑ ሌላ የምህንድስና ሙያ የተማረ መኮንን ስላልነበረ ክፍሉ በሚገባ ያልተደራጀ መሆኑን ገልጸዋል። ሆኖም ግን እርሳቸው ክፍሉ ውስጥ ተመድበው ስራ ከጀመሩ በኋላ የምህንዲስና ሙያ ስልጠና ወስደው በመመለስ ተዋጊ መሐንዲስ ክፍሉን ለማደራጀት ጥረት አድርገው እንደነበር አስረድተዋል።

በተዋጊ መሐንዲስ ክፍል ውስጥ ጥቂት ዓመት እንደሰሩ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ለውጊያ

መረጃ (Combat Intelligence Training) ስልጠና ተመርጠው ወደ አዲስ አበባ ሄደው ስልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ 3ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ተመልሰው በመሄድ በመረጃ ስራ ማገልገላቸውን አስረድተዋል። በመረጃ ስራ አገልግሎት ላይ እያሉ እንደገና የጂኦግራፊና የካርታ ንባብ (Geography and Map Reading Training) ስልጠና እድል አግኝተው በደብረዘይት ስልጠና መውሰዳቸውን ገልጸዋል። በስልጠናው ወቅት በርካታ የመስክ ልምምዶችን በደብረዘይት፤ በናዝሬትና በአዲስ አበባ አከባቢዎች እየተዘዋወሩ በመስራት ጥልቀት ያለው የካርታ ንባብ እውቀት ቀስመው እንደተመለሱ አስረድተዋል። የካርታ ንባብ ስልጠናቸውን እንደ ጨረሱም ወደ 3ኛ ክፍለ ጦር ተመልሰው በመረጃ አገልግሎት ሰርተዋል። የካርታ ንባብና የመረጃ ስልጠና በፈጠረላቸው መልካም አጋጣሚ ከስራቸው ጋር ወቅታዊ ሁኔታዎችንና (Current Affairs) የዓለም ዜናዎችን እየተከታተሉ ከመረጃ ጋር በማቀናበር ለክፍሉ አዛዥና ለጦር መኮንኖች ያቀርቡ እንደነበር በትዝታ ያስታውሳሉ።

የውጊያ መረጃዎችን የሚሰበስቡት ትናንሽ አውሮፕላኖችን እየተጠቀሙ በተለያዩ የኦጋዴን አከባቢዎች እየተዘዋወሩ ቅኝት በማካሄድ ነበር። ይህም የካርታ ንባብ እውቀታቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዳዳበረው ተናግረዋል። በዚህ ልምዳቸውም ከ1960-1965 ዓ.ም በኮንጎ ውስጥ በተካሄደው ጦርነት የተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪ ጦር አካል ከነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሚስዮን ጋር ኮንጎ በመዝመት ከፍተኛ አገልግሎት ማበርከታቸውን ገልጸዋል። ወደ ኮንጎ የተጓዙት በቀጥታ ከድሬዳዋ ተነስተው ወደ ኮንጎ ኪንሻሳ በመብረር ነበር። ከኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ጦር ጋር ኮንጎ እንደ ደረሱም ካርታ ንባብ እውቀታቸውን በመጠቅም የአየር ቅኝት እያካሄዱ ስለ ጠላት ጦር እንቅስቃሴ መረጃ እየሰበሰቡ ለወገን ጦር ወቅታቂ መረጃ በመስጠት እንዳገለገሉ ገልጸዋል።

የኮንጎ ግዳጃቸውን ፈጽመው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ አሁንም 3ኛ ክፍለ ጦር ውስጥ አሰበተፈሪ በሚገኘው ጦር ክፍል ውስጥ በመረጃና በዘመቻ *(Combat Intelligence and Operations)* ስራ ተመድበው እንደሰሩ ተናግረዋል። አሰበተፈሪ ስራ ላይ እያሉ እርሳቸውና ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ለአሰልጣኝነት ተመርጠው ወደ ሐረር ጦር አካዳሚ በመሄድ ለረጅም ዓመታት በአሰልጣኝነት ማገልገላቸውን ተናግረዋል። በአካዳሚ ቆይታቸው ወቅት ለረጅም

ዓመታት ያከበቱትን የካርታ ንባብ ትምህርት በዘመናዊ መልክ በማደራጀት ለእጩ መኮንኖች ስልጠና መስጠት እንደ ጀመሩ ተናግረዋል። በአካዳሚው ውስጥ እጩ መኮንኖች የካርታ ንባብ እውቀትን ከወታደራዊ ስልት (Map Reading and Military Tactics) ጋር አጣምረው እንዲማሩ በማድረግ የተሟላ የካርታ ንባብና ወታደራዊ ስልት እውቀት ያላቸው ብቁ መኮንኖች ማፍራት እንደተቻለ በኩራት ይናገራሉ።

ሐረር ጦር አካዳሚ ውስጥ አሰልጣኝ ሆነው እያገለገሉ እያሉ የካፍተኛ ትምህርት እድል አግኝተው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቅቀው በጂኦግራፊ የመጀመሪያ ዲግሪ (B.A in Geography) ተመርቀዋል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተመረቁ በኋላ በሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት የእጩ መኮንኖች አሰልጣኝ በመሆን አገልግለዋል። ሆሌታ ገነት እያሉ ሌላ የድህረ ምረቃ ትምህርት እድል እግኝተው ወደ አሜሪካ ከተላኩ በኋላ ትምህርታቸውን እስከ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ትምህርት ተከታትለው በዶክቶሬት ዲግሪ (PHD) ተመርቀዋል። ከምረቃ በኋላ መኖሪያቸውን በሰሜን አሜርካ አድርገው በተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች ውስጥ በከፍተኛ የሃላፊነት ደረጃ መስራታቸውን በትዝታ አጫውተውናል።




ዶር/ሻለቃ ዮሐንስ አባተ

**ለ.** ሁለተኛው የእለቱ ፕሮግራም “ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር

በሰሜን አሜሪካ  የተመሰረተበት 25ኛ ዓመት መታሰቢያ ልዩ ዝግጅት ነበር። በእለቱ የምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ የተመሰረተበት 25ኛ ዓመት በልዩ ሁኔታ ታስቦ ውሏል። ፕሮግራሙ የተዘጋጀውና ይፋ የሆነው ለአባላቱ በቅድሚያ ሳይነገር በድንገተኛ (surprise) ነበር። "ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ" የተመሰረተው በጁን ወር 2001 ዓ.ም (እ.አ.አ) ነበር። 25ኛውን ዓመት መታሰቢያ ቀን ለማክበር እቅድ ተይዞ የነበረው በጁን ወር 2026 ነበር። ነገር ግን በአንዳንድ የፋይናንስና የአስተዳደር ችግሮች ምክንያት በእቅዱ መሰረት በሰኔ ወር ማክበር አልተቻለም። ሆኖም ግን ማህበሩ የተመሰረተበት 25ኛ ዓመት በደመቀ ሁኔታ ማክበር ባይቻልም ቢያንስ ዓመቱ ሳይታሰብ መታለፍ እንደሌለበት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስላመነበት በልዩ ሁኔታ ተከብሮ እንዲውል  ተስማምቶ ኦገስት 9 ቀን 2026 ዓ.ም በተካሄደው የአሉምናይ ማህበሩ መደበኛ ስብሰባ ቀን በልዩ ዝግጅት ታስቦ ውሏል።

የመታሰቢያ ቀኑን አስመልክቶ የማህበሩ ሊቀ መንበር ኮሎኔል ጋተው ተፈሪ ባደረጉት የመግቢያ ንግግር የማህበሩን የ25 ዓመታት ጉዞ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ከገለጹ በኋላ ማህበሩን ለከፍተኛ ስኬት ያበቁ የቀድሞ አመራር አባላትን በስም በመጥቀስ አመስግነዋል። ማህበሩን በሊቀ መንበርነት፤ በጸሐፊነት፤ በገንዘብ ያዥነትና በሂሳብ አያያዝ በታማኝነት ላገለገሉ አባላት ያላቸውን ከፍተኛ ከበሬታና አድናቆት ከመግለጻቸው በላይ ማህበሩን በወንድማዊ ፍቅር፤ በጥበብና በማስተዋል እንዲሁም በከፍተኛ ትእግስት አመራር በመስጠት አንድነቱን የጠበቀ የአካዳሚ ቤተሰብ ለመፍጠር የተጫወቱትን ጉልህ ሚና በአድናቆት ገልጸዋል። በንግግራቸው ማጠቃለያም በሰዓት ውስንነት ምክንያት ማህበሩ በሃያ ዓመት ጉዞው ያከናወናቸውን ተግባራት በዝርዝር ማቅረብ ባይቻልም ያካናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና ያጋጠመው ተግዳሮት ሳይጠቀስ መታለፍ እንደሌለበት በአጽናኦት ገልጸዋል።

ስለሆነም ቀኑ በሁለት ዋና ጉዳዮች ታስቦ ውሏል፦

1. ልዩ ፕሮግራሙ የተጀመረው የምሩቃን ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ 2026 ዓ.ም ድረስ በሞት ለተለዩን አባላት የአንድ ደቂቃ ሂሊና ጸሎት በማድረግ

ነበር። ከሰኔ 2001_ሰኔ 2026 ዓ.ም በሞት የተለዩት የማህበሩ አባላት የሚከተሉ ናቸው፦ ብ/ጄኔራል ለገሰ ተፈራ (7ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል ካሳዬ ክፍሌ (6ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል ጀማል አባገሮ (7ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል መለስ ወልደዮሐንስ (6ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል ተረፈ ወልደተንሳይ፤ ኮሎኔል ይግዛው አብርሃ (2ኛ ኮርስ)፤ ኮሎኔል ንጉሱ ተፈራ (16ኛ ኮርስ)፤ ሻለቃ ብርሃኑ ወልደተንሳይ፤ ሻለቃ ሚካኤል ዘወልድ (2ኛ ኮርስ)፤ ሻለቃ ክንፈሚካኤል ከፈኒ (21ኛ ኦርስ)፤ መ/አለቃ ዳምጤ ይልማ (16ኛ ኮርስ)፤ ሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ (3ኛ ኮርስ)፤ ሻምበል አበረ በላይ (5ኛ ኮርስ)፤ ሻምበል ተስፋሚካኤል ወልደዮሐንስ፤ ሻምበል ከበደ መካሻ፤ ሻምበል ፍቅረየሱስ ስዩም፤ መ/አለአ መስፍን ክብረት (13ኛ ኮርስ)፤ መ/አለቃ ባንታምላክ ይመኑ (14ኛ ኮርስ)፤ ወይዘሮ አስቴር አበበ (የሻለቃ ሙሉጌታ ባለቤት)፤ ወይዘሮ አስቴር አሰፋ (የሻለቃ/ዶ/ር ዮሓንስ አባተ ባለቤት)፤ ወይዘሮ ዘውዲቱ (የሻለቃ ሸዋረጋ ባለቤት)፤ ሲስተር እየሁብርሃን ይመኑ (የመ/አለቃ ባንታምላክ ይመኑ እህት)፤ ወይዘሮ ወርቅአፈስ ሙሉጌታ (የሻለቃ በዛብህ-7ኛ ኮርስ ባላቤት።

2. ሁለተኛ ማህበሩን ለመመስረት አባላትን ከማሰባሰብና ከማስተባበር ጀምሮ ማህበሩን በማቋቋም፤ አመራር በመስጠት፤ በገንዘብና በማቴሪያል ድጋፍ ከፍተኛ አስተጿኦ ላበረከቱ አባላትና ግለሰቦች የእውቅና ምስክር ወረቅት ተዘጋጅቶ ነበር። በመሆኑም የቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበርን ለመመስረት አባላትን በማሰባሰብና ብማሳመን፤ በማደራጅትና ማህበሩን በማቋቋምና እንዲሁም ደከመኝ፤ ሰለቸኝ ሳይሉ፤ ጊዚያቸውን፤ ገንዘባቸውንና እውቀታቸውን መስዋእት በማድረግ 25 ዓመት በመምራት ለውጤት ላበቁና በመሰጠት ላገለገሉ የአመራር አባላትና ማህበሩን በገንዘብና በቁሳቁስ ለረዱ የሁለተኛ ትውልድ የምሩቃን ልጆች የእውቅና ምስክር ወረቅት ተሰጥቷል።



**3.** የጦር አካዳሚ ምሩቃን ማኅበር በሰሜን አሜሪካ በ**25** ዓመት ጉዞ ያከናወናቸው ተግባራትና ያጋጠመው ተግዳሮት

የቀዳማዊ ኃይለሰላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ በ1950 ዓ.ም በቀዳማዊ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የተቋቋመ ወታደራዊ ሳይንስ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ተቋም) ነበር። አካዳሚው የሶስት ዓመት ወታደራዊና አካዳሚክስ ስልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቶ 21 ኮርሶችን ካስመረቀ በኋላ በ1969 ዓ.ም በወታደራዊ አስተዳደር መንግስት (ደርግ) በድንገት ተዘግቷል። የአካዳሚ ምሩቃን በተመረቁበት ወታደራዊ ሙያ አገራቸውን በታላቅ መስዋእትነት ሲያገለግሉ ቆይተው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግምባር (ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ) መንግስት ስልጣን ይዞ የቀድሞ ሰራዊትን ሲበትን የምሩቃኑም አገልግሎት አብቅቶ ከሰራዊቱ ለመገለል በቅተዋል። ምሩቃኑ ከሰራዊቱ ከተበተኑ በኋላ በተማሩት ሙያ ስራ ሰርተው ራሳቸውንና አገራቸውን መርዳት እንዳይችሉ በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግስት እገዳ ስለ ተጣለባቸው አብዛኞቹ ያለ ምንም ስራ አገር ውስጥ ሲቀመጡ ሌሎች ደግሞ ወደ ተለያዩ ውጭ አገራት ለመሰደድ ተገደዋል። በስደት አገራቸውን ለቀው ከወጡት መካከል ለአብዛኞቹ የአሜሪካ መንግስት በሰጠው ጥገኝነት አሜሪካ መጥተው ኑሮ ሲመሰርቱ ሌሎች ደግሞ በአውሮፓና በተለያዩ ዓለም አገራት በስደት ይኖራሉ።

ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመጡት የአካዳሚ ምሩቃን መካከል አብዛኞቹ በዋሽንግተን ዲ.ሲ፤ በሜሪላንድና በቨርጂኒያ ስቴቶች ውስጥ ኑሮ መስርተው እየኖሩ ነው። በሰሜን አሜሪካ ኑሮ ከመሰረቱ በኋላ ምሩቃኑ እርስ በእርስ ለመጠያየቅና ለመረዳዳት ያስችላቸው ዘንድ በሰኔ ወር 1993 ዓ.ም (ጁን 2001 እ.አ.አ) “ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ማህበር” መመስረት ችለዋል። ማህበሩን የማቋቋም ሃሳብ የመነጨውና ለውጤት የበቃው ለአካዳሚው ቅን አመለካከትና ምንጊዜም የማይደበዝዝ ፍቅር ባላቸው የአካዳሚ ምሩቃን ጥረት ነው። ይህ በጥቂት ግለሰቦች አስተባባርነትና ብልህ አመራር የተደራጀው አንድነት ጉልበት አግኝትና ለውጤት በቅቶ በአሉምናይ ማህበር ደረጃ የተመሰረተው ጁን 2001 ዓ.ም ነበር። መስራች አባላቱ ሃያ አንድ (21) ሲሆኑ ዛሬ ቁጥራቸው አድጎ ከስድሳ (60) በላይ አባላት አሉት።

ማህበሩ የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ያለው፤ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመራና መደበኛ ተግባሩን የሚያከናውኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የተለያዩ ንኡስ ኮሚቴዎች አሉት። ኮሚቴዎቹ በበጎ ፍቃደኝነት የሚሰሩና የአገልግሎት ዘመናቸውም በመተዳደሪያ ደንቡ የተገደበ ነው። ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሚከተሉት አባላት ማህበሩን በሥራ አስፈጻሚነት አገልግለዋል። ሌሎች አሁንም በማገልገል ላይም ናቸዉ።

- ሻለቃ ኃይለማሪያም አባይ ሊቀ መንበር
- “ ሚካኤል ዘወልድ “
- “ ሙሉጌታ ከበደ “
- ኮሎኔል ጋተዉ ተፈሪ ሊቀ መንበር
- “ ገበየሁ ኦስማን ጸሐፊ
- ሌ/ኮሎኔል አፈወርቅ ንጋቱ “
- ሻምበል በዙ ወ/ሚካኤል ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ
- ሻለቃ ገ/ሚካኤል ሔራሞ ጸሐፊ
- “ ተዘራ በዛብህ ሂሳብ ሹም
- መ/ አ አህመድ መሐመድ ገንዝብ ያዥ

በሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲ.ሲ የተቋቋመው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር *(Haileselassie/Harar Military Academy Alumni Association-HMAHAA)* በዋሽንግተን ዲ.ሲ አስተዳደር አትራፊ ባልሆነ ድርጅትነት *(Non-Profit Organization)* የተመዘገበና ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው። ማህበሩ አትራፊ ድርጅት ባለመሆኑ ለተለያዩ ወጪዎች የሚከፈለው ገንዘብ የሚገኘው የማህበሩ አባላት በየወሩ በፈቃደኝነት ከሚያዋጡት መዋጮ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ የማህበሩ አባል በየወሩ $ 25.00 እያዋጣ በማበሩ ባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ ይሆናል። ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥም እንደ ሁኔታው አባላት ተጨማሪ ገንዘብ እንዲያዋጡ ይጠየቃሉ። የሰሜን አሜሪካው የአካደሚ ምሩቃን ማህበር ከተመሰረተ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የአካዳሚ ምሩቃንም የራሳቸውን መተዳደሪያ ደንብ ቀርጸው *ጥቅምት 28 ቀን 1997 ዓ.ም (ኖቬምበር 8 ቀን 2004 እ.አ.አ)* የኢትዮጵያውን ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበርን መስርተዋል። በመሆኑም ሁለቱ እህት ማህበራት የአንድ ጦር አካዳሚን ዓላማ የሚጋሩ በመሆናቸው የቀረበ ግንኙነት በመፍጠር በምክክርና በመረዳዳት መንፈስ በመስራት ላይ ይገኛሉ።

### **3.1** የአሉምናይ ማህበሩ ዓላማና ያከናዎናቸው ዋና ዋና ተግባራት

#### **3.1.1.** የማህበሩ ዓላማ

የጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበሩ በሰሜን አሜሪካ ከተመሰረተ 25 ዓመታትን አስቆጥሯል። ማህበሩ የተቋቋመው ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ዋና ዋና ዓላማዎች መሰረት አድርጎ ነው፦

ሀ. የአካዳሚ ምሩቃንን አንድ ላይ በማሰባሰብና እርስ በእርስ በማቀራረብ በሃዘንና በደስታ ጊዜ እንዲጠያየቁና እንዲረዳዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ለ. የአካዳሚ ምሩቃን ሚስቶችና ልጆቻቸው *(Second Generation Youth)* በአካዳሚ ማህበር ዓላማ ስር ተሰባስበውና ተደራጅተው የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል ታሪኩን እንዲያቆዩ ማደፋፈር፤ ልጆች የራሳቸውን ማህበር እንዲያቋቁሙ ምክር መስጠትና አስፈላጊውን እርዳታ ማድረግ፤

ሐ. በሕይወት ያሉትና የሌሉት የአካዳሚ ምሩቃን ለአገር ነጻነት ያበረከቱትን ገድሎች መዝግቦ የአካዳሚን ታሪክ በመጻፍ ለምሩቃኑ ልጆችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ፤

መ. አንድ የማህበር አባል በሞት ሲለይ ወይም ቤተሰቡ ውስጥ የሞት አደጋ ሲያጋጥም የገንዘብ እርዳታ ማድረግ፤ ከቤተሰቡ ጋር በመተባበር የቀብር ስነ-ስርዓት ማስፈፈጸም የሚሉ ናቸው።

**3.1.2** ከምስረታው ጀምሮ ማህበሩ ያከናወናችው ተግባራት

የአካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ በሃያ አምስት ዓመታት ጉዞው የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፦

- በየሁለት ወሩ ተከታታይ መደበኛ ስብሰባዎችን እያካሄደ አባላትን እርስ በእርስ ያገናኛል፤ አባላት በሚያጋጥማቸው ችግሮች ዙሪያ ውይይት በማድረግ ጠቃሚ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል። የውይይት አጀንዳዎቹ በአብዛኛው በገንዘብ ነክ፤ በእርዳታና በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው።

- አንድ የማህበር አባል ሲሞት ወይም ቤተሰቡ አባል ላይ የሞት አደጋ ሲያጋጥም የገንዘብ እርዳታ ያደርጋል፤ የቀብር ስነ-ስርዓት ያስፈጽማል። በዚህም አባላት የሚፈለግባቸውን መዋጮ በየወሩ ያለ ማቋረጥ ስለ ሚከፍሉ አስፈላጊው እርዳታ ያለ ምንም ችግር ሲፈጸም ቆይቷል። አባላት ሙሉ ፈቃደኝነት በማሳየታቸውና ንቁ ተሳትፎ በማድረጋቸው ማህበሩ ጽኑ መሰረት ላይ ቆሞ ስኬታማ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። ይህን በማድረጋቸው መላ አባላት ምስጋና የሚገባቸው ናቸው።

- ማህበሩ የራሱ መሰብሰቢያ አደራሽ ስለሌለው የምሳ መስተንግዶን ጨምሮ በየሁለት ወሩ የስብሰባ ስፍራ የሚያዘጋጁት አባላት ናቸው። ይህም ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው

ባወጣው ቅደም ተከተል መሰረት አባላት መስተንግዶውንና የስብሰባውን ቦታ ስለሚያዘጋጁ ስብሰባው ሳይስተጓጎል በመካሄድ ላይ ይገኛል።

- መደበኛ ስብሰባዎቹ አባላትና ቤተሰብ የሚገናኙበት፤ የአካዳሚ ትዝታዎችና አዝናኝ ቀልዶች እየተነሱ አባላት የሚዝናኑበት አጋጣሚ ስለሆነ ሁሌም በናፍቆት የሚጠበቅ ቀን ነው።

- በህይወት ያሉና የሌሉ የአካዳሚ ምሩቃን ሚስቶች፤ ልጆቻቸው፤ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው ጭምር የሚሳተፉበት ማህበር ስለሆነ ስብሰባዎቹ ሁሉን አካታችና አስደሳች ናቸው።

- ሁለተኛው ትውልድ (Second Generation Children) የሆኑት የምሩቃን ልጆች ከተሳትፎ ባለፈ ማህበሩን በመደገፍ ረገድ እያደረጉ ያለው አስተዋጽኦም እጅግ አበረታችና ጉልህ ቦታ የሚሰጠው ነው። እነዚህ የምሩቃን ልጆች የማህበሩ ጀርባ አጥንት በመሆን እያደርጉ ያለው ድጋፍ አበረታችና በጣም የሚደነቅ ነው። እስከ አሁን ላደረጉት ድጋፍ ማህበሩ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረበ እርዳታቸው ወደፊትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል የዘወትር ምኞቱ ነው።

## 3.2 የማህበሩ ስኬትና ተግዳሮቶች

### ሀ. የማህበሩ ስኬት

ማህበሩ የተመሰረበትን ዓላማ ተግባራዊ ከማድረጉ አኳያ አባላትንና ቤተሰቦቻቸውን አንድ ላይ አሰባስቦ ጠንካራ የአካዳሚ ቤተሰብ መፍጠር ችሏል። በዚህ ምክንያት አባላት እርስ በእርስ በመገናኘትና ህብረት በመፈጠር በሃዘንና በደስታ ጊዜ መረዳዳት መቻላቸው ትልቅ ስኬት ነው። ማህበሩ ራሱን ከማጠናከር አልፎ አዲስ አበባ ለሚገኘዉ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ማህበር ከምስረታው ጀምሮ የገንዘብ እርዳታ በማድረግ ወንድማዊ አጋሪነቱን በተግባር አሳይቷል። ከማህበሩ እርዳታ ሌላ አባላት በግላቸው በተለያዩ ጊዜያት ለአዲስ አበባው ማህበር የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ሰጥተዋል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ

ለሚካሄደው የደን ልማት ፕሮግራም ማህበሩ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የማይናቅ አስተውጻኦ አድርጓል። በአጠቃላይ ማህበሩ ከአርባ (40) ጊዜ በላይ ለተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ በጎ ተግባር ፈጽሟል። የሰሜን አሜሪካ የጦር አካዳሚ አሉምናይ ማህበር በመንግስት እውቅና ያገኘና ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማህበር እንደ መሆኑ የገንዘብ አቅም ሲፈቅድና ሁኔታዎች ሲመቻቹ ወደ "አካዳሚ ፋውንዴሽን" የማደግ እድሉ ሰፊ ነው። አቅሙ ሲጠናከርም የሰበዓዊ አገልግሎቱን ዘርፍ በማስፋት በልማትና በግብረ ሰናይ ስራዎች ጉልህ አስተዋጻኦ እንደ ሚኖረው እምነታችን ጽኑ ነው።

ለ. የማህበሩ ተግዳሮት

የሰሜን አሜሪካ ምሩቃን ማህበር ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ስኬታማ ሲሰራ ቢቆይም የራሱ የሆኑ ተግዳሮቶች አሉት። በመጀመሪያ ደረጃ ማህበሩ የራሱ ጽ/ቤትና መሰብሰቢያ አዳራሽ የለውም። ማህበሩ የራሱ ጽ/ቤትና የስብሰባ አዳራሽ ስለሌለው ከላይ እንደ ተጠቀሰው በየሁለት ወሩ የሚያካሄደውን ስብስባ የሚያዘጋጅት አባላት በራሳቸው የግል ወጪ ነው። እያንዳንዱ አስተናጋጅ በራሱ ተነሳሽነትና ፈቃደኝነት የስብሰባ አዳራሽና የመስተንግዶ ምሳ ወጪ ችሎ ስብሰባዎችን ሲያስተናግድ ቆይቷል። ይህም በየጊዜ እየጨመረ ከመጣው የኑሮ ውድነትና የዋጋ መናር ጋር ከፍተኛ ጫና እንደሚፈጥር እሙን ነው። ነገር ግን አባላት ለአካዳሚው ካላቸው ከፍተኛ ፍቅር የተነሳ ለማህበሩ ቅድሚያ በመስጠት ስብሰባው እንዳይተጓጎል የሚያደርጉት ጥረት በጣም የሚደነቅ መስዋእትነት ነው። ከፍተኛ ምስጋናም ይገባቸዋል። ምንም እንኳን ማህበራችን ዓላማውን ቢያሳካም አንዲት ቢሮ እንኳን ስለሌላው የማህበሩ ንብረትና ዶኩሜንቶች የሚቀመጡት በየስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ቤት ውስጥ ነው። ይህም ማህበሩ በእቅድና በፕላን ስራውን እንዳያከናዉን ትልቅ እንቅፋት እየፈጠረ ስለሆነ ችግሩን ለማቃለል አስቸኳይ መፍጥሔ መፈለግ ግድ ይሆናል።

4. በመጨረሻም ከዚህ ቀጥሎ ስማቸው ለተዘረዘሩት የማህበሩ አመራር አባላትና ማህበሩን በገንዘብ፤ በሙያቸውና በቁሳቁስ እርዳታ ድጋፍ ላደረጉ የምሩቃኑ ሁለተኛ ትውልድ ልጆች በማህበሩ የተዘጋጀው የእውቅና ምስክር ወርቀት ተሰጥቷል።

የእውቅና ምስክር ወረቀቱ በሁለት የተከፈለ ሲሆን፦

ሀ. የመጀመሪያው እውቅና ምስክር ወረቅት ማህበሩን በአመራርና በተለያዩ ሙያ ላገለገሉ አባላት የተዘጋጀ ሽልማት ነው።




ሻለቃ ሃይለማርያም አባይ



የሻለቃ ሚካኤል ዘወልድ ባለቤት ወይዘሮ ሙሉና ልጃቸው ዶ/ር ጽዮን ሚካኤል




የሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ ልጅ ዶ/ር ቅድስት ሙሉጌታ




ኮሎኔል ገበየሁ ኦስማንና ባላቤታቸው ወይዘሮ የምስራች ደምሴ




ሌ/ኮሎኔል አፈወርቅ ንጋቱ




ሻምበል በዙ ወልደሚካኤል

ኮሎኔል/ዶ/ር ጌታቸው አፍሬ  (በስብሰባ ያልተገኙ)

ለእነዚህ ተሸላሚዎቹ የእውቅና ምስክር ወረቀቱን የሰጡት የማህበራቻን አባልና የአካዳሚ አንደኛ ኮርስ ምሩቅ ብ/ጄኔራል መኮንን ገብረማርያም ናቸው።



ብ/ጄኔራል መኮንን ገ/ማርያም (1ኛ ኮርስ) እና ባለቤታቸው ወይዘሮጽላተሙሴ

ለ. ሁለተኛው የእውቅና ምስክር ወረቀት የተሰጠው በሙያ፤ በገንዘብና በቁሳቁስ ለማህበሩ ድጋፍ ላደረጉ የአካዳሚ ምሩቃን ልጆች ነው።




አንተነህ ንጉሱ (የኮሎኔል ንጉሱ ተፈራ-16ኛ ኮርስ) ልጅ

ዳንኤል ገብረመስቀል (የብ/ጄኔራል ገብረመስቀል አዝብጤ-12ኛ ኮርስ) ልጅ

(ስብሰባ አልተገኙም)




ወይዘሮ ጽዮን ንጉሴ (የሻለቃ ኑሴ ሞገስ 21ኛ ኮርስ) ልጅ

ኢንጂነር ይስሐቅ ኡኩሞ (የኮሎኔል ኡኩሞ ሻታ-16ኛ ኮርስ) ልጅ (በስብሰባ አልተገኙም)

ለእነዚህ ተሸላሚዎች የምስክር ወረቀቱን የሰጡት የማህበራችን መስራች አባል፤ የመጀመሪያው ሊቀ መንበርና የአካዳሚ አንደኛ ኮርስ ምሩቅ ሻለቃ ሃይለማርያም አባይ ናቸው።





ሻለቃ ሃይለማርያም አባይ (1ኛ ኮርስ) ሽልማት ሲሰጡ

ፕሮግራሙ የተዘጋጀው በድንገተኛ ስለሆነ የእውቅና ሽልማቱ አጠቃላይ አባላትን አካታች አለመሆኑን እንረዳለን። በተለይም ከምስረታው ጀምሮ የማህበሩን አባላት በማሰባሰብ ፤ በገንዘብና በቴክኒክ ድጋፍ ከፍተኛ አስተዋጻኦ ያበረከቱ አባላት እንዳሉ እናምናለን። በተለይም ማህበራችን ጠንካራ መሰረት ላይ እንዲቆም ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ሴቶች እህቶቻችን ባለመካተታቸው ሽልማቱን ጎዶሎ እንደ ሚያደርገው እንረዳለን። ነገር ግን ለሁሉም በአንድ ጊዜ ሽልማት ማዘጋጀት ባይቻልም ጉልህ ድርሻ ላበረከቱ አባላት በሙሉ ወደፊት ሽልማቱ በእቅድ እንደሚቀጥል እምነታችን ጽኑ ነው። የማህበሩ ስኬት የእያንዳንዱ አባል የግል ትብብር ውጤት ስለሆነ ጅማሮው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አንጠራጠርም።

በመጨረሻም የመታሰቢያ ቀኑ ባማረ ሁኔታ ታስቦ እንዲውል ሻምበል በዙ ወልደሚካኤልና ዶ/ር ሙሉእመቤት በስፋት ያዘጋጁት መስተንግዶ ብዙ ሰዎች የተገኙበትን አጋጣሚ ፈጥሯል። በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀው ምግብና መጠጡ ለመታሰቢያ በዓሉ ልዩ ድምቀት የሰጠ በመሆኑ አዘጋጆቹን ከልብ እናመሰግናለን። በእለቱ ስብሰባ ከ13ኛና ከ17ኛ ኮርሶች በስተቀር ከአንደኛ እስከ 21ኛ ኮርስ ያሉት ምሩቃንና ቤተሰብ አባላት መገኘታቸው ቀኑን ልዩ አድርጎታል። በመጨረሻም የእለቱን መስተንግዶ ከጣፋጭ ምግብና መጠጥ ጋር በጥሩ ሁኔታ ላዘጋጁት ሻምበል በዙ ወልደሚካኤልና ዶ/ር ሙሉእመቤት እንዲሁም ለመላው ቤተሰባቸው ምስጋና በማቅረብ የእለቱ ስብሰባ በ5፡00 ሰዓት ተጠናቋል። የሚቀጥለው መስተንግዶ አዘጋጅ የሻለቃ ሚካኤል ዘወልድ ባለቤት ወይዘሮ ሙሉ ገብረጻዲቅ ናቸው።

የሰብሰባው ተሳታፊዎች በከፊል




Maison
Perrier


EXIT



코리안커뮤니티센터
K-COMMUNITY CENTER
K-COMMUNITY CENTER